# የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) ጠቅላላ ጉባዔ

## የመጀመሪያ አስቸኳይ ስብሰባ

## የአቋም መግለጫ

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) ጠቅላላ ጉባዔ የመጀመሪያ አስቸኳይ ጉባዔውን በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ከሚገኙ የምርጫ ወረዳዎች የተወከሉ የፓርቲው አባላት በተገኙበት መስከረም 22 እና 23 ቀን 2014 ዓ.ም አካሂዷል። ጉባዔው በተለያዩ ሀገራዊ እና ድርጅታዊ ጉዳዮች ላይ ሲወያይ ቆይቶ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ውሳኔዎች አሳልፏል።

1. ፓርቲው ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በተሰጠው አቅጣጫ መሠረት ምርጫ 2013 በተካሄደ በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ የደንብ ማሻሻያ እንዲያደርግ በመጠየቁ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ ጠርቶ ሰፊ ውይይት ካደረገ በኋላ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ እንዲሻሻሉ የተሰጡ የመተዳደሪያ ደንብ አንቀፆች እና ባለፉት አመታት ሊያሰሩ አልቻሉም የተባሉ የተለያዩ የመተዳደሪያ ደንቡ አንቀፆችና ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች ላይ የቀረበውን ማሻሻያ በ595 ድጋፍ፣ 3 ተቃውሞ እና 32 ድምጸ ተዓቅቦ አፅድቆ የተሻሻለው ደንብ ለብሔራዊ ምርጫ ቦርድ እንዲገባ ውሳኔ ተላልፏል።

2. የብሔራዊ ምክር ቤት እንዲቋቋም ከጉባዔው የተነሳውን ሀሳብ በ131 ድጋፍ፣ 484 ተቃውሞ እና 32 ድምጸ ተዓቅቦ ውድቅ ተደርጓል።

3. በፓርቲው ፕሮግራም ላይ የቀረበውን የቅርጽ እና የአቀራረብ ማሻሻያ ምክ ረ ሀሳብ በተባበረ ድምጽ ተቀብሎ አጽድቋል።

4. በግጭት ውስጥ ካሉ አካባቢዎች የመጡ የጉባኤው አባላት በአካባቢያቸው ያለውን ሁኔታ እና ችግሩ ከተከሰተ አንስቶ እስካሁን የነበረውን ሂደት ለጉባዔ ተሳታፊዎች አስረድተዋል። የጉባዔው አባላትም የችግሩ ምንጭ የሆነውን ዘውግን መሰረት ያደረገ የፖለቲካ መስመርን ለመቀየር እና በመላው የሀገራችን አካባቢዎች የሚኖሩ ሁሉም ዜጎች እኩል መብታቸው ተከብሮ መኖር የሚችሉበት የፖለቲካ ሥርዓት እንዲመሠረት የተቻላቸውን እደሚያደርጉ እና የሚፈለገውን መስዕዋትነት ለመክፈል ያላቸውን ቁርጠኝነት አረጋግጠዋል።

5. ከምርጫ 2013 ጋር በተያያዘ በፓርቲው የመንግሥት ዘርፍ የተዘጋጀውን ሪፖርት አዳምጦ የተገኙ በጎ ልምዶች እና የነበሩ ክፍተቶች ላይ ከተወያየ በኋላ ፓርቲው ሀገራችን አሁን ከገባችበት ውስብስብ እና አደገኛ ሁኔታ ወጥታ አንድነቷን ለማረጋገጥ እና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እዲመሰረት የሚያግዙ የውስጠ-ፓርቲ አቅም ግንባታ እና ጠንካራ ሀገራዊ

ተቋማት መገንባት ላይ ትኩረት አድርጎ እዲሰራ ውሳኔ አስተላልፏል፡፡

6. ከገዢው ፓርቲ የቀረበውን የአብረን እንሰራ ጥያቄ በሚመለከት ጉባዔው ሰፊ ጊዜ ወስዶ ከተወያየ በኋላ አሁን ሀገራችን ካለችበት ወቅታዊ ሁኔታ አንፃር ጥያቄውን ተቀብሎ አብሮ ለመስራት በ536 ድጋፍ፣ 79 ተቃውሞ እና 25 ድምጸ ተዓቅቦ በአብላጫ ድምጽ ውሳኔ አስተላልፏል፡፡

በጉባዔው የመዝግያ ዝግጅት ላይ የሀገር ሽማግሌዎች፣ የኃይማኖት አባቶች፣ የሲቪክ ማህበረሰቡ አባላት እና የተለያዩ የፖለቲካ ፓርቲ ተወካዮች ተገኝተው ለኢዜማ ያላቸውን አጋርነት አሳይተው የሁለት ቀን ጉባዔው በደመቀ ሁኔታ ተጠናቋል፡፡